የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፲
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፭ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 10
ADDIS ABABA 24th December 2012

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፸፫/፪ሺ፭ ዓ.ም.

የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………………………………ገጽ ፮ሺ፮፻፸፰
ሠንጠረዥ……………………………………ገጽ ፮ሺ፯፻፫

## CONTENTS

**Regulation No. 273/2012**

Trademark Registration and Protection Council of Ministers Regulation…………………………………… Page 6678
Schedule ……………………………………Page 6703

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፸፫/፪ሺ፭

## ስለንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር ፭፻፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፵፯ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፸፫/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "አዋጅ" ማለት የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር ፭፻፩/፲፱፻፺፰ ነው፤

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

፫/ "ጽሕፈት ቤት" ማለት የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ነው፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 273 /2012

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION ON TRADEMARK REGISTRATION AND PROTECTION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 47 of the Trademark Registration and Protection Proclamation No. 501/2006.

### PART ONE
### GENERAL

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Trademark Registration and Protection Council of Ministers Regulation No. 273/2012".

**2. Definitions**

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "Proclamation" means the Trademark Registration and Protection Proclamation No.501/2006;

2/ the definitions provided for under Article 2 of the Proclamation shall also be applicable to this Regulation;

3/ "Office" means the Ethiopia Intellectual Property Office;

፬/ "ወኪል" ማለት በዚህ ደንብ መሠረት በጽሕፈት ቤቱ የተመዘገበ የንግድ ምልክት ወኪል ነው፤

፭/ "የምዝገባ ባለቤት" ማለት የንግድ ምልክት በጽሕፈት ቤቱ ዘንድ ያስመዘገበ ሰው ነው፤

፮/ "የንግድ ምልክትን በጥቅም ላይ ማዋል" ማለት የንግድ ምልክቱን በዕቃዎቹ ወይም በዕቃዎቹ በማሸጊያ ወይም መለያ ምልክት ላይ መለጠፍ፣ የንግድ ምልክቱ ከዕቃዎቹ ጋር በቅርበት ሆኖ እንዲታይ ማድረግ፣ የንግድ ምልክቱን በዕቃዎቹ ወይም አገልግሎቶቹ ማስታወቂያ ወይም የማስተዋወቂያ ማቴሪያሎች ላይ መጠቀም ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በንግድ ምልክቱና በዕቃዎቹ ወይም በአገልግሎቶቹ መካከል ግንኙነት መፍጠር ነው፤

፯/ "ማሳተም" ማለት በአዕምሯዊ ንብረት ጋዜጣ ወይም ሰፊ ሀገራዊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ማሳተም ወይም በጽሕፈት ቤቱ ድረገጽ ላይ መጫን ነው፤

፰/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፱/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት
## ከጽሕፈት ቤቱ ጋር ስለሚደረጉ ግንኙነቶች

### ፫. በጽሑፍ ስለመገናኘት

፩/ ከጽሕፈት ቤቱ ጋር የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት በጽሑፍ መሆን አለበት።

፪/ በጽሕፈት ቤቱ የሚወሰድ ማንኛውም እርምጃ በጽሑፍ በተያዙ የጽሕፈት ቤቱ መዝገቦች ላይ ብቻ መመሥረት ይኖርበታል። በቃል የተደረጉ መግባባቶች፣ መተማመኛዎችና ግንኙነቶች በጽሕፈት ቤቱ ላይ አስገዳጅነት አይኖራቸውም።

### ፬. ሰነዶች የሚቀርቡበት ቋንቋ

፩/ ለጽሕፈት ቤቱ የሚቀርብ የንግድ ምልክት ምዝገባ ወይም ማንኛውንም በመታየት ላይ ያለን ጉዳይ የተመለከተ ማመልከቻ አካል የሆነ ማንኛውም ሰነድ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጀ መሆን ይኖርበታል።

፪/ ማንኛውም በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ያልተዘጋጀ ሰነድ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ተተርጉሞና ከዋናው ሰነድ ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል።

4/ "agent" means a trademark agent registered by the Office in accordance with this Regulation;

5/ "registration owner" means a person who has registered a trademark with the Office;

6/ "use of a trademark" means attaching the trademark to the goods or packaging or labeling of the goods, displaying the trademark closely associated with the goods, placing the trademark in advertising or promotional material for the goods or services, or in any other way establishing a relationship between the trademark and the goods or the services;

7/ "publish" means publication in the Intellectual Property Gazette or a newspaper having nationwide circulation or by means of uploading at the Office web site;

8/ "person" means any natural or legal person;

9/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO
## COMMUNICATING WITH THE OFFICE

### 3. Written Communications

1/ Any communication with the Office shall be in writing.

2/ The Office's action shall be based exclusively on the written records in the Office. Oral understandings, stipulations and communications may not be binding upon the Office.

### 4. Language for Documents

1/ Any document filed with the Office forming part of an application for registration of a trademark or any proceedings in the Office shall be in the Amharic or English language.

2/ Any document that is in a language other than Amharic or English shall be accompanied by a translation into Amharic or English.

፫/ ጽሕፈት ቤቱ ትክክለኛ ትርጉም መስሎ ያልታየውን ማንኛውንም ትርጉም ሳለመቀበልና ተስተካክሎ እንዲቀርብ ሰነዱን ለአመልካቹ ሊመልስለት ይችላል፡፡

፬/ ጽሕፈት ቤቱ ከአማርኛ ወይም ከላቲን በተለየ ፊደል የተጻፈ ቃል ያካተተ ሰነድ ሲቀርብለት የቃሉ ገላጭ ሃሳብ ወይም ትርጉም እንዲቀርብለት ሊያደርግ ይችላል:: ገላጭ ሃሳቡ ወይም ትርጉሙ ቃሉ ከምን ቋንቋ እንደተገኘ መግለጽና በአመልካቹ ወይም በአመልካቹ ወኪል መፈረም አለበት::

## ፭. ግንኙነት የሚደረግበት አድራሻና ጉዳዩን ለይቶ ስለመግለጽ

፩/ ከጽሕፈት ቤቱ ጋር የሚደረግ ማንኛውም የጽሑፍ ግንኙነት የጽሕፈት ቤቱን ትክክለኛ ስምና አድራሻ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

፪/ የጽሑፍ ግንኙነቱ እንደአግባቡ የንግድ ምል ክቱን፣ የአመልካችን ስምና አድራሻ፣ ማመልከ ቻው ገቢ የሆነበትን ቀን፣ የማመልከቻውን ወይም ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ የተሰጠውን ቁጥር፣ የምዝገባ ባለቤቱን፣ የምዝገባውን ቁጥር እና የምዝገባውን ቀን የሚያመለክት መሆን ይኖርበታል፡፡

፫/ ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገውን የማያሟላ ሰነድ ለላኪው ሊመልስለት ይችላል፡፡

፬/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ (፫) ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ተመላሽ የተደረገ ሰነድ:-

ሀ) ከተመለሰበት ቀን ጀምሮ በ፴ ቀናት ውስጥ ተስተካክሎ በድጋሚ ከቀረበ መጀመሪያ በቀረበበት ቀን ለጽሕፈት ቤቱ ገቢ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፤ ወይም

ለ) ከ፴ ቀናት በላይ ዘግይቶ ተስተካክሎ በድጋሚ ከቀረበ በድጋሚ በቀረበበት ቀን ለጽሕፈት ቤቱ ገቢ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

## ፮. ሰነዶችን ስለመረከብና መለያ ቁጥር ስለመስጠት

፩/ ጽሕፈት ቤቱ በተረከባቸው ሰነዶች ላይ ሰነዶቹ ገቢ የሆኑበትን ቀንና ሰዓት የያዘ ማህተም ማድረግና ሰነዶቹን ስለመቀበሉ ማረጋገጫ መስጠት አለበት፡፡

፪/ ጽሕፈት ቤቱ ለዚሁ ጉዳይ ባወጣው መመሪያ መሠረት በኤሌክትሮኒክ መገናኛ ዘዴ አማካኝ ነት ሰነድ የተቀበለ እንደሆነ በኤሌክትሮኒክ መሣሪያው ላይ የተመዘገበው ቀንና ሰዓት ጽሕፈት ቤቱ ሰነዱን የተቀበለበት ቀንና ሰዓት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

3/ The Office may refuse to accept any translation which, in its opinion, is inaccurate and return the document to the applicant for correction.

4/ Where a document contains a word in characters other than Amharic or Latin, the Office may require a transliteration or translation of such word and the statement regarding a transliteration or translation shall state the language to which the word belongs and shall be signed by the applicant or the applicant's agent.

## 5. Addressing Communications and Identification of Subject Matter

1/ Any written communication with the Office shall properly express the name and address of the Office.

2/ A written communication shall, as may be appropriate, identify the trademark, the name and address of the applicant, the filing date, the application or the proceeding number, the registration owner, the registration number and the registration date.

3/ The Office may return to the sender any document that does not comply with sub-article (1) and (2) of this Article.

4/ If a document returned pursuant to Article 4 (3) of this Regulation or sub-article (3) of this Article is rectified and re-submitted to the Office:

a) within 30 days from the date of return, it shall be treated as received on its former date of submission; or

b) after a delay of more than 30 days, it shall be treated as received on the actual date of re-submission.

## 6. Receipt and Marking of Documents

1/ The Office shall stamp the date and hour of receipt on a document that is filed and acknowledge receipt of same.

2/ When the Office accepts the filing of documents by means of the electronic media in accordance with directive issued for such purpose, the time and date of receipt registered by the electronic device shall be considered the official time and date of receipt of the document by the Office.

፫/ ጽሕፈት ቤቱ ለተረከበው ማመልከቻ የመለያ ቁጥር መስጠትና የማመልከቻው አካል በሆነው እያንዳንዱ ሰነድ ላይ የመለያ ቁጥሩን ማስፈር አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ለማመልከቻ የተሰጠ መለያ ቁጥር ማመልከቻውን አስመልክቶ በቀጣይ በሚደረጉ የጽሑፍ ግንኙነቶች ሁሉ የሚጠቀስ ይሆናል፡፡

## ፯. በፖስታ ቤት ሰነዶችን ስለመላክ

፩/ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መቅረብ የሚገባው ሰነድ ጊዜው ከማለፉ ከአምስት ቀናት አስቀድሞ በአስቸኳይና በተመዘገበ ፖስታ ለጽሕፈት ቤቱ የተላከ ከሆነ ለጽሕፈት ቤቱ የጊዜ ገደቡ ካለፈ በኋላ የደረሰው ቢሆንም እንኳ በወቅቱ እንደ ቀረበ ይቆጠራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ የንግድ ምልክትን ለማስመዝገብና የንግድ ምልክት ምዝገባን ለማሳደስ በሚቀርቡ ማመልከቻዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## ፰. ተመላሽ ስለማይደረጉ ሰነዶች

፩/ በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ ወይም ጽሕፈት ቤቱ ባወጣው መመሪያ በግልጽ ካልተመለከተ በስተቀር ለጽሕፈት ቤቱ ገቢ የተደረገ ሰነድ ተመላሽ አይደረግም፤ ሆኖም ጽሕፈት ቤቱ በጽሑፍ ጥያቄ ከቀረበለት ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል የሰነዱን ኮፒ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪/ ዋናውን ሰነድ ለጽሕፈት ቤቱ ገቢ ያደረገ ሰው ፎቶ ኮፒውን በማስቀረት ዋናውን ሰነድ መውሰድ ይችላል፡፡

# ክፍል ሦስት

# የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

## ፱. የማመልከቻ አቀራረብ

የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ በአዋጁ አንቀጽ ፰ ከተመለከቱት በተጨማሪ ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-

፩/ አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ቅጅ እና ፈራሚው ድርጅቱን ወክሎ ለመፈረም የሚያስችል ሥልጣን ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፤

፪/ ማመልከቻው በወኪል አማካይነት የቀረበ ከሆነ የወኪሉ የምዝገባ የምስክር ወረቀትና በአግባቡ የተረጋገጠ የውክልና ሥልጣን ማስረጃ፤

3/ The Office shall assign a reference number to an application it receives and mark each document constituting the application with the assigned reference number.

4/ The reference number assinged to an application under sub-article (3) of this Article shall be referred to in all subsequent communications concerning the application.

## 7. Filling Documents by Mail

1/ A document sent to the Office via express and registered postal mail five days before the expiry of a specified deadline shall be considered as being timely filed despite it is received by the Office after the deadline.

2/ The provision of sub-article (1) of this Article may not apply with regard to the application for registration and renewal of trademarks.

## 8. Documents not Returnable

1/ Unless expressly provided in the Proclamation, this Regulation or directive issued by the Office, documents submitted to the Office may not be returned; provided, however, that copies of same document may be given upon written request and payment of the applicable fee.

2/ Any person who has submitted an original document to the Office may take back the original one by replacing the copy thereof.

# PART THREE
# APPLICATION FOR REGISTRATION OF TRADEMARK

## 9. Submission of Application

An application for registration of a trademark shall be accompanied by the following documents in addition to those specified under Article 8 of the Proclamation:

1/ if the applicant is a legal person, copy of the certificate of its registration and evidence authorizing the person who has signed the application to represent the legal person;

2/ if the application is filed through an agent, the certificate of registration of the agent and a duly authenticated power of attorney;

፫/ የንግድ ምልክቱ ስዕላዊ ከሆነ ወይም ሥዕላዊ ነገሮች ካሉት የእነዚሁ አጠር ያለ የጽሑፍ መግለጫ፤

፬/ ምልክቱ ከአማርኛ ወይም ከላቲን ፊደል ወይም ከአማርኛ፣ ከአረብኛ ወይም ከላቲን ቁጥር የተለየ የሌላ ቋንቋ ፊደል ወይም ቁጥር የያዘ እንደሆነ አቻ የአማርኛ ወይም የላቲን ፊደል እና አቻ የአረብኛ ቁጥር የያዘ መግለጫ፤

፭/ አመልካቹ የቀለም ቅንጅትን እንደ ንግድ ምልክት ወይም የንግድ ምልክቱ መለያ ባህሪ አድርጎ የሚወስደው ከሆነ ባለቀለሙን የንግድ ምልክት ሦስት ኮፒዎች እና በምልክቱ ውስጥ እያንዳንዱ ቀለም የሚገኝበትን ቦታ ጭምር የሚገልጽና አመልካቹ የንግድ ምልክቱ የቀለም ቅንጅት ወይም መለያ ባህሪው ነው የሚልበትን ምክንያት የያዘ መግለጫ።

## ፲. የወል የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ

የወል የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ስለንግድ ምልክቱ አጠቃቀም ከሚደነግግ መተዳደሪያ ደንብ ሁለት ቅጂዎች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።

## ፲፩. የንግድ ምልክት ስዕላዊ መግለጫ

፩/ የንግድ ምልክት ስዕላዊ መግለጫ ከአመልካቹ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ የዋለውን ወይም ጥቅም ላይ ለማዋል የታሰበውን የንግድ ምልክት በትክክል የሚወክል መሆን ይኖርበታል።

፪/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፫ መሠረት የቀዳሚነት መብት ለመጠየቅ የሚቀርብ ማመልከቻ የሆነ እንደሆነ የንግድ ምልክቱ ስዕላዊ መግለጫ አመልካቹ በሚገኝበት ሀገር በተገቢው ሁኔታ ተመዝግቦ በተሰጠው የምዝገባ የምስክር ወረቀት ላይ የተቀመጠውን የንግድ ምልክት በትክክል የሚወክል መሆን ይኖርበታል።

## ፲፪. በማመልከቻ ላይ የሚደረግ ማሻሻያ

፩/ አመልካች ጽሕፈት ቤቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፭(፩) መሠረት ምዝገባውን ስለመቀበሉ ማስታወቂያ ከመላኩ እና የተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ ከማሳተሙ በፊት በማንኛውም ጊዜ ማመልከቻውን ለማሻሻል ጽሕፈት ቤቱን በጽሁፍ መጠየቅ ይችላል።

3/ a brief written description of pictures, if the trademark is pictorial or includes pictorial elements;

4/ where the trademark contains characters other than Amharic or Latin, or numerical expressions other than Amharic, Arabic or Latin numerals their transliteration into Amharic or Latin characters and Arabic numerals;

5/ if the applicant claims a combination of colors as a trademark or distinctive feature of the trademark, three copies of the trademark in color and the explanation that the applicant claims a combination of color as the trademark or as a distinctive feature, which includes a description of position of appearance of each color in the trademark.

## 10. Application for Registration of Collective Trademark

An application to be submitted for the registration of a collective trademark shall, in addition to those specified under Article 9 of this Regulation, be accompanied by two copies of a statute governing the use of the trademark.

## 11. Graphical Representation of Trademark

1/ The graphical representation of a trademark shall be the exact representation of the trademark used or intended to be used in connection with the applicant's goods or services.

2/ If the application is lodged in accordance with Article 13 of this Regulation seeking priority, the graphical representation shall be the exact representation of the trademark as it appears in the registration certificate of a trademark duly registered in the country of origin of the applicant.

## 12. Amendment of Application

1/ An applicant may request the Office in writing at any time before the issuance of notice of acceptance for registration and publication for call of opposition under Article 25(1) of this Regulation to amend his application.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የቀረበ የማሻሻያ ጥያቄ፡-

ሀ) ዋናው ማመልከቻ ገቢ በተደረገበት ጊዜ በነበረው በንግድ ምልክቱ ባህሪ ወይም በንግድ ምልክቱ ሥዕላዊ መግለጫ ላይ መሠረታዊ ለውጥ የሚያመጣ ከሆነ፤ ወይም

ለ) ዋናው ማመልከቻ ገቢ በሆነበት ጊዜ ከተካተቱት የዕቃዎችና የአገልግሎቶች ዝርዝር ውስጥ ሌላ ተጨማሪ ዕቃ ወይም አገልግሎት ለማካተት ከሆነ፤

ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪)(ሀ) በተመለከተው መሠረት ጽሕፈት ቤቱ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን የማሻሻያ ጥያቄው ተቀባይነት እንደሌለው ከተገለጸለት ቀን ጀምሮ በ፷ ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

፲፫. የቀዳሚነት መብት

በአዋጁ አንቀጽ ፲ መሠረት የቀዳሚነት መብትን ለመወሰን ቀደም ሲል በውጭ ሀገር የቀረበ ማመልከቻ ገቢ የተደረገበት ቀን ለጽሕፈት ቤቱ የቀረበ የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ገቢ እንደተደረገበት ቀን ተደርጎ ሊወሰድ የሚችለው፡-

፩/ የቀድሞው ማመልከቻ የኢንዱስትሪያዊ ንብረት ጥበቃ የፓሪስ ኮንቬንሽን ተዋዋይ ወገን በሆነ ሀገር ወይም የፓሪስ ኮንቬንሽን ከሚሰጠው የቀዳሚነት መብት ጋር ተመሳሳይ ውጤት ያለው መብት ለአመልካች በሚሰጥ ሀገር ማመልከቻው በተገቢው ሁኔታ ገቢ የሆነ እንደሆነ፤ እና

፪/ አመልካቹ የንግድ ምልክት ምዝገባው ማመልከቻ ለጽሕፈት ቤቱ ገቢ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፺ ቀናት ውስጥ የቀድሞውን ማመልከቻ የተረጋገጠ ኮፒ ወይም የቀድሞው ማመልከቻ ገቢ በሆነበት ሀገር የተሰጠ የቅድሚያ መብት የምስክር ወረቀት ለጽሕፈት ቤቱ ያቀረበ እንደሆነ፤

ነው፡፡

## ክፍል አራት

## ማመልከቻን ስለመመርመር

፲፬. ስለፎርማሊቲ ምርመራ

፩/ ጽሕፈት ቤቱ ማመልከቻ ሲቀርብለት በአዋጁ አንቀጽ ፰ እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ የፎርማሊቲ ምርመራ ያካሂዳል፡፡

2/ An application submitted under sub-article (1) of this Article shall be rejected if the amendment:

a) substantially alters the character or pictorial representation of the trademark shown in the original application; or

b) is to make additions in the list of goods or services included in the original application.

3/ Any applicant dissatisfied with the decision of the Office on rejection of application in accordance with sub-article (2)(a) of this Article, may appeal to the court having jurisdiction within 60 days after the receipt of the decision.

13. **Priority Right**

For the purposes of establishing priority right in accordance with Article 10 of the Proclamation, the date an earlier application filed in a foreign country shall be treated as the date an application submitted to the Office for registration of a trademark if:

1/ the earlier application was duly filed in a country that is a party to the Paris Convention for the Protection of Industrial Property or in a country that grants a right of priority to an applicant that has equivalent effect to the right of priority provided for by the Paris Convention; and

2/ the applicant submits to the Office, within 90 days from the filing date of the application for registration of the trademark, a certified copy of the earlier application or a priority certificate issued by the country where the previous application was filed.

## PART FOUR

## EXAMINATION OF APPLICATION

14. **Formality Examination**

1/ The Office shall, undertake formality examination on the application submitted to verify its compliance with the requirements of Article 8 of the Proclamation and Article 9 of this Regulation.

፪/ ማመልከቻው በአዋጁ አንቀጽ ፰ እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ የተመለከቱትን መመዘኛዎች የማያሟላ ከሆነ ጽሕፈት ቤቱ አመልካቹ ሊያሟላ የሚገባውን መመዘኛዎች አሟልቶ ማስታወቂያው ከተላከበት ቀን ጀምሮ ከ፺ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለጽሕፈት ቤቱ ገቢ እንዲያደርግ በጽሑፍ ያስታውቀዋል፡፡

፫/ አመልካቹ በጽሕፈት ቤቱ እንዲያቀርብ የተጠየቀውን እርማቶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ገቢ ካላደረገ፣ ጽሕፈት ቤቱ ማመልከቻውን ውድቅ ያደርገዋል፡፡ አመልካቹ የከፈለው የገንዘብ ክፍያ ካለም ተመላሽ አይደረግለትም፡፡

፬/ ማመልከቻው በአዋጁ አንቀጽ ፰ እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ የተመለከቱትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ከሆነ ጽሕፈት ቤቱ ማመልከቻውን ለምርመራ ስለመቀበሉ ለአመልካቹ ያሳውቀዋል፡፡

፲፭. በመታየት ላይ ያሉ ማመልከቻዎች ዝርዝር

፩/ ጽሕፈት ቤቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬ መሠረት የፎርማሊቲ ምርመራ አሟልተው በመታየት ላይ ያሉ ማመልከቻዎችን ዝርዝር አዘጋጅቶ ይይዛል፡፡

፪/ ዝርዝሩ የሚከተሉትን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡-

ሀ) የእያንዳንዱን አመልካች ስምና አድራሻ፤

ለ) ማመልከቻ የቀረበበት የእያንዳንዱ የንግድ ምልክት መግለጫ ወይም ቅጂ፤

ሐ) እያንዳንዱ ማመልከቻ የሚሸፍናቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶችና የምደባ ቁጥራቸውን፤

መ) እያንዳንዱ ማመልከቻ ገቢ የሆነበትን ቀንና ሰዓት፤ እና

ሠ) ጽሕፈት ቤቱ ለእያንዳንዱ ማመልከቻ የሰጠውን ቁጥር፡፡

፲፮. የሥረ-ነገር ምርመራ

፩/ ጽሕፈት ቤቱ፡-

ሀ) ማመልከቻ የቀረበለት የንግድ ምልክት በአዋጁ አንቀጽ ፭ መሠረት ለምዝገባ ብቁ መሆኑን፤ ወይም

ለ) ምዝገባው በአዋጁ አንቀጽ ፮ ወይም አንቀጽ ፯ መሠረት መከልከል ያለበት መሆኑን፤

ለመወሰን በቀረበለት የንግድ ምዝገባ ማመልከቻ ላይ የሥረ-ነገር ምርመራ ያከናውናል፡፡

2/ Where the Office finds that the requirements of Article 8 of the Proclamation and Article 9 of this Regulation are not fulfilled, it shall notify the applicant, in writing, to file the necessary correction within 90 days from the date of the notification.

3/ If the applicant does not file the required correction within the time limit, the Office shall reject the application and the applicant shall forfeit the fees paid, if any.

4/ Where the Office finds that the requirements of Article 8 of the Proclamation and Article 9 of this Regulation are fulfilled, it shall acknowledge, by a notice to the applicant, acceptance of the application for examination.

**15. Index of Pending Applications**

1/ The Office shall prepare and maintain an Index of pending applications which meet the formality requirements pursuant to Article 14 of this Regulation.

2/ The Index shall include:

a) the name and address of each applicant;

b) a description or reproduction of each applied-for mark;

c) the goods or services each application covers and their classification number;

d) the date and time when each application was filed; and

e) the number that the Office assigned to each application.

**16. Substantive Examination**

1/ The Office shall conduct substantive examination on the application for registration of a trademark to decide on:

a) eligibility of the trademark for registration in accordance with Article 5 of the Proclamation; or

b) refusal of registration in accordance with Article 6 or Article 7 of the Proclamation.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በማመልከቻ ላይ የሥረ-ነገር ምርመራ የሚያከናውነው፡-

ሀ) ለዚሁ ተግባር በጽሕፈት ቤቱ የወጣውን መመሪያ በመከተል ማመልከቻ የቀረበለትን ምልክት በመገምገም፤ እና

ለ) የተመዘገቡ ምልክቶች እና በመታየት ላይ ያሉ ማመልከቻዎችን በተመለከተ በጽሕፈት ቤቱ መዛግብት የሠፈሩ መረጃዎችን በመፈተሽ፤

ይሆናል።

፫/ ማንኛውም ሰው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ በመፈጸም የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ከማቅረቡ በፊት ቀደም ሲል ተመሳሳይ የንግድ ምልክት አለመመዝገቡን ለማረጋገጥ ፍተሻ እንዲደረግለት መጠየቅ ይችላል።

## ፲፯. ተመሳሳይ የንግድ ምልክቶችን ለማስመዝገብ ስለሚቀርቡ ማመልከቻዎች

ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ማመልከቻዎች የሚመሳሰሉ የንግድ ምልክቶችን ለአንድ ዓይነት ወይም ለተመሳሳይ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ለማስመዝገብ በአንድ ቀን ለጽሕፈት ቤቱ ከቀረቡና የቀደምትነት መብት ለማንኛውም ተፈፃሚ የማይሆን ከሆነ፡-

፩/ ጽሕፈት ቤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ቀድሞ ጥቅም ላይ የዋለውን የንግድ ምልክት ለአዋጁ አንቀጽ ፯ ዓላማ እንደ ቀዳሚ የንግድ ምልክት ሊቆጥረው ይችላል፤ ወይም

፪/ ከቀረቡት የንግድ ምልክቶች መካከል አንዱም በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ ከሆነ በጊዜ ቅደም ተከተል መጀመሪያ ማመልከቻ የቀረበለት የንግድ ምልክት ለአዋጁ አንቀጽ ፯ ዓላማ ቀዳሚ ምልክት እንደሆነ ይቆጠራል።

## ፲፰. በጽሕፈት ቤቱ ስለሚወሰድ እርምጃ

ጽሕፈት ቤቱ ባደረገው የሥረ-ነገር ምርመራ፡-

፩/ አመልካቹ በአዋጁ አንቀጽ ፭ መሠረት የተወሰኑ ተጨማሪ መሥፈርቶችን ማሟላት የሚገባው ሆኖ ካገኘው፤ ወይም

፪/ የንግድ ምልክቱ ምዝገባ በአዋጁ አንቀጽ ፮ ወይም አንቀጽ ፯ መሠረት ሊከለከል የሚገባው ሆኖ ካገኘው፤

ይህንኑ ከነምክንያቱ ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

## ፲፱. ለጽሕፈት ቤቱ እርምጃ መልስ ስለመስጠት

፩/ አመልካቹ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፲፰ መሠረት ለተሰጠው ማስታወቂያ ማስታወቂያው ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ፺ ቀናት ውስጥ መልሱን ለጽሕፈት ቤቱ በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል።

2/ The substantive examination of an application under sub-article (1) of this Article shall be carried out:

a) by evaluating the trademark in accordance with the directive issued by the Office for such purpose; and

b) through search of the records of the Office for registered trademarks and pending applications.

3/ Any person, before filing an application for registration of a trademark, may apply for search to know whether the trademark applied for is registered or not upon payment of the fee prescribed in the Schedule attached hereto.

## 17. Applications for Registration of Similar Trademarks

When two or more applications are submitted to the Office on the same day for the registration of similar trademarks for identical or similar goods or services and there is no priority right applicable to any of them:

1/ the Office may treat the trademark used in Ethiopia first as an earlier trademark for the purpose of Article 7 of the Proclamation; or

2/ if neither trademark has been used in Ethiopia, the trademark applied first in terms of time shall be treated as an earlier trademark for the purpose of Article 7 of the Proclamation.

## 18. Action of the Office

If the Office, as the result of the findings of the substantive examination:

1/ requires the applicant to satisfy certain additional requirements in accordance with Article 5 of the Proclamation; or

2/ concludes that the trade mark is inadmissible for registration pursuant to Article 6 or 7 of the Proclamation;

it shall notify same to the applicant, in writing, together with the reasons thereof.

## 19. Response to Action of the Office

1/ The applicant shall respond to the Office within 90 days from the date of receipt of the notice in accordance with Article 18 of this Regulation.

፪/ አመልካቹ በሚሰጠው መልስ፡-

ሀ) የተጠየቀውን ተጨማሪ መሥፈርት ለማሟላት ወይም ለምዝገባው እንቅፋት የሆኑትን ምክንያቶች ለማስወገድ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ፤ ወይም

ለ) በዚህ ደንብ ማመልከቻ ማሻሻልን አስመልክቶ የተቀመጠው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተጠቀሱትን እርምጃዎች ለመውሰድ በማመልከቻው ላይ ማሻሻያ ለማድረግ መጠየቅ፤

ይችላል።

፫/ ጽሕፈት ቤቱ የአመልካቹ መልስ እንደደረሰው ማመልከቻውን እንደገና ይመረምራል።

## ፳. የመልስ መስጫ ጊዜን ስለማራዘም

፩/ አመልካቹ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፱ የተደነገገው የጊዜ ገደብ በበቂ ምክንያት እንዲራዘምለት የጊዜ ገደቡ ከማለቁ በፊት በጽሑፍ ሲጠይቅና ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ ሲፈጽም ሊራዘምለት ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የጊዜ ገደቡ ሊራዘም የሚችለው የመልስ መስጫ የጊዜ ገደብ ከሚያበቃበት ጊዜ ጀምሮ ለተከታታይ ፺ ቀናት ይሆናል፤ ሆኖም ከሁለት ጊዜ በላይ ሊራዘም አይችልም።

፫/ ጽሕፈት ቤቱ የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄው የተፈቀደ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

## ፳፩. ማመልከቻን ውድቅ ስለማድረግ

፩/ አመልካቹ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፱ መሠረት የሰጠው መልስ እንደቀረበ ማመልከቻው እንደገና ተመርምሮ በተገኘው ውጤት አመልካቹ የተጠየቁትን ተጨማሪ መሥፈርቶች ሙሉ በሙሉ አለማሟላቱ ወይም ለምዝገባው እንቅፋት የሆኑ ምክንያቶችን ለማስወገድ አለመቻሉ የተረጋገጠ እንደሆነ ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻውን ውድቅ ያደርጋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰጠ ውሳኔ ለአመልካቹ በጽሑፍ መድረስና የምዝገባ ማመልከቻው ውድቅ የተደረገባቸውን ምክንያቶች መግለጽ አለበት።

፫/ የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻው ውድቅ የተደረገበት አመልካች የጽሕፈት ቤቱ ውሳኔ በደረሰው ፷ ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

2/ The applicant in his response may:

a) take proper measure to satisfy the specified additional requirements or to overcome the grounds impeding the registration; or

b) request amendment to the application, subject to the limitation provided for in this Regulation, with a view to taking the measures referred to in paragraph (a) of this sub-article.

3/ The Office shall re-examine the application upon receipt of the applicant's response.

## 20. Extension of Time to Respond

1/ The time limit stipulated in Article 19 of this Regulation may be extended, if the applicant requests, in writing, by providing sufficient reasons for the extension before the expiry of the time limit and upon payment of the fee prescribed in the Schedule attached hereto.

2/ The time limit may be extended, pursuant to sub-article (1) of this Article, for a period of consecutive 90 days following the expiry of the applicable response period; provided, however, that such extension may not be allowed for more than twice.

3/ The Office shall notify its decision to the applicant in writing whether the extension is granted or not.

## 21. Rejection of Application

1/ An application for registration of a trademark shall be rejected by the Office if the re-examination of the application upon receipt of the applicant's response under Article 19 of this Regulation shows that the applicant fails to fully satisfy the specified additional requirements or to overcome the grounds impeding the registration.

2/ Decision of the Office under sub-article (1) of this Article shall be communicated to the applicant in writing stating the reasons for the rejection.

3/ Any applicant whose application for registration of a trademark is rejected may appeal to the court having jurisdiction within 60 days from receipt of the decision of the Office.

## ፳፪. ማመልከቻ ውድቅ ከተደረገ በኋላ በአመልካቹ ስለሚወሰድ እርምጃ

አመልካቹ የይግባኝ ጊዜው ከማለፉ በፊት ሳይሟሉ የቀሩ መስፈርቶችን ለማሟላት ወይም ለምዝገባው እንቅፋት የሆኑ ምክንያቶችን ለማስወገድ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ ወይም እነዚህን እርምጃዎች ለመውሰድ ማመልከቻውን ማሻሻል ይችላል።

## ፳፫. የተተወ ማመልከቻ

፩/ ጽሕፈት ቤቱ በሚከተሉት ምክንያቶች አንድን ማመልከቻ እንደተተወ ይቆጥረዋል፦

ሀ) ማመልከቻው እየታየ ባለበት ወቅት በማንኛውም ጊዜ አመልካቹ ለጽሕፈት ቤቱ በጽሁፍ በማሳወቅ ማመልከቻውን የተወ እንደሆነ፤

ለ) አመልካቹ ለጽሕፈት ቤቱ ውሳኔ መልስ መስጠት የነበረበት ጊዜ ወይም የተራዘመው የመልስ መስጫ ጊዜ ሳያበቃ መልስ ያልሰጠ እንደሆነ ወይም ሳይሟሉ የቀሩትን መስፈርቶች ለማሟላት ወይም ለምዝገባው እንቅፋት የሆኑትን ምክንያቶች ለማስወገድ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ያልወሰደ ወይም እነዚህን እርምጃዎች ለመውሰድ ማመልከቻውን ያላሻሻለ እንደሆነ፤

ሐ) በጽሕፈት ቤቱ ውሳኔ ላይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ የነበረበት ጊዜ ያለፈበት እንደሆነ፤ ወይም

መ) ይግባኝ አቅርቦ ይግባኙ ውድቅ የሆነበት እንደሆነ።

፪/ ማመልከቻው የተተወ እንደሆነ ጽሕፈት ቤቱ በመዝገቡ ላይ "የተተወ" የሚል ምልክት በማድረግ በተተው መዝገቦች ፋይል ውስጥ እንዲቀመጥ ያደርጋል።

## ፳፬. መርማሪ ከመሆን ስለመነሳት

ማንኛውም ለንግድ ምልክት ምዝገባ የቀረበ ማመልከቻን እንዲመረምር በጽሕፈት ቤቱ የተመደበ ሰው፦

፩/ ከአመልካቹ ወይም ከወኪሉ ጋር የቅርብ ዝምድና ያለው ሆኖ ሲገኝ፤

፪/ በንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻው ላይ ጥቅም ያለው ሲሆን፤ ወይም

፫/ ከአመልካቹ ወይም ከወኪሉ ጋር ያለው ማንኛውም ሌላ ዓይነት ግንኙነት ከአድሎ ነጻ የሆነ ምርመራ እንዳያካሂድ ተጽኖ ሊያሳድር የሚችል ሆኖ ሲገኝ፤

በራሱ አነሳሽነት ወይም በአመልካቹ ወይም በሌላ ጉዳዩ በሚመለከተው ወገን በሚቀርብ ጥያቄ ከምርመራ ኃላፊነቱ እንዲነሳ ይደረጋል።

## 22. Applicant Action after Rejection

Prior to the expiry of the period of appeal on the rejection, the applicant may take measures to satisfy the outstanding requirements or overcome the grounds impeding the registration or amend the application to take such measures.

## 23. Abandoned Application

1/ The Office shall treat an application as abandoned if:

a) the applicant expressly withdraws the application by a written notice at any time during the proceeding;

b) the applicant fails to respond to the decision of the Office before the expiry of the response period or authorized extension or to take measures to fully satisfy outstanding requirements or to overcome grounds impeding registration or amend the application with a view to taking such measures;

c) the applicant fails to appeal to the court having jurisdiction against the decision of the Office before the expiry of the appeal period; or

d) the applicant's appeal is unsuccessful.

2/ When the application is abandoned, the Office shall mark the file "ABANDONED" and place it in the records of abandoned files.

## 24. Exclusion from Being Examiner

Any person assigned by the Office to examine an application for registration of a trademark shall, on his own initiative or upon the request of the applicant or any other interested party, be excluded from exercising his function where, he:

1/ is a close relative of the applicant or his agent;

2/ has an interest in the application for registration of the trademark; or

3/ has such other kinds of relations with the applicant or his agent that might influence the impartial examination of the application.

## ክፍል አምስት
## የንግድ ምልክት ምዝገባን ስለመቃወም

### ፳፭. የንግድ ምልክት ለምዝገባ ብቁ መሆንን ስለማሳወቅ

ጽሕፈት ቤቱ ማመልከቻ የቀረበለት የንግድ ምልክት፡-

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፯ ወይም አንቀጽ ፲፱(፫) መሠረት የተደረገ ምርመራን ወይም ድጋሚ ምርመራን፤ ወይም

፪/ ሳይሟሉ የቀሩ መስፈርቶችን ሙሉ በሙሉ ለማሟላት ወይም ለምዝገባው እንቅፋት የሆኑ ምክንያቶችን ለማስወገድ አመልካቹ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፪ መሠረት የወሰዳቸውን እርምጃዎች፤

ተከትሎ ለምዝገባ ብቁ ሆኖ ካገኘው የንግድ ምልክቱን ለተቃውሞ ጥሪ ሕትመት ማዘጋጀትና ማመልከቻው ለምዝገባና ለተቃውሞ ጥሪ ተቀባይነት እንዳለው ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት፡፡

### ፳፮. የተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ ስለማውጣት

፩/ ጽሕፈት ቤቱ፡-

ሀ) የአመልካቹን ስምና አድራሻ፤

ለ) የንግድ ምልክቱን ሥዕላዊ መግለጫ፤

ሐ) ማመልከቻው የሚሸፍናቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች እና የምደባ ቁጥራቸውን፤

መ) እንደአግባቡ ማመልከቻው ገቢ የሆነበትን ቀን ወይም የቀዳሚነት መብት ቀን፤

ሠ) የማመልከቻውን ቁጥር፤

ረ) የብቸኛ ተጠቃሚነት መብት ያለመጠየቅ መግለጫ ተሰጥቶ ከሆነ ይህንኑ፤ እና

ሰ) አመልካቹ ወኪል ካለው ስምና አድራሻውን፤

በማካተት የንግድ ምልክቱን ምዝገባ የሚቃወም ቢኖር እንዲቀርብ በአዋጁ አንቀጽ ፲፪ መሠረት በአመልካቹ ወጪ የተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ ያሳትማል፡፡

፪/ አመልካቹ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፭ የተመለከተው ማስታወቂያ በደረሰው ፷ ቀናት ውስጥ የተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያውን ማሳተሚያ ካልከፈለ ማመልከቻውን እንደተወው ተቆጥሮ የዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፫(፪) ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆንበታል፡፡

### ፳፯. የንግድ ምልክት ምዝገባን ስለመቃወም

፩/ ለምዝገባ የቀረበውን የንግድ ምልክት ለመቃወም የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በጽሕፈት ቤቱ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት የተቃውሞ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡

## PART FIVE
## OPPOSITION TO REGISTRATION OF TRADEMARK

### 25. Notification of Eligibility of Trademark for Registration

If the Office determines that the trademark applied for is eligible for registration following:

1/ the examination or re-examination of the application in accordance with Article 17 or Article 19(3) of this Regulation; or

2/ the measures taken by the applicant to fully satisfy the outstanding requirements or to overcome the grounds impeding the registration pursuant to Article 22 of this Regulation;

it shall arrange for publication of the trademark for opposition and notify the applicant the acceptance of the application for registration purpose and publication for call of opposition.

### 26. Publication of Notice for Call of Opposition

1/ The Office shall publish, at the expense of the applicant pursuant to Article 12 of the Proclamation, a notice for call of opposition to the registration of the trademark that includes:

a) the applicant's name and address;

b) the graphic representation of the trademark;

c) the goods or services the application covers and their classification number;

d) the filing date of the application or right of priority date, as may be appropriate;

e) the application number;

f) the disclaimer, if any; and

g) the name and the address of the applicant's agent, if applicable.

2/ If the applicant fails to pay the amount of money required to cover the expenses of publishing the notice for call of opposition, within 60 days from the date of receipt referred to in Article 25 of this Regulation, the application for registration of the trademark shall be considered as abandoned and be treated in accordance with Article 23(2) of this Regulation.

### 27. Opposition to Registration of Trademark

1/ Any person who intends to oppose the registration of a trademark may submit his statement of opposition to the Office by filling the form prescribed by the Office for such purpose.

፪/ የተቃውሞ ማመልከቻው ከሚከተሉት ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት:-

ሀ) ተቃውሞው የተመሠረተባቸውን ምክንያቶች የሚደግፉ ማስረጃዎች፤

ለ) በዚህ ደንብ የተወሰነው ክፍያ መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፤

ሐ) ተቃውሞው የቀረበው በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል ከሆነ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ቅጅ እና ፈራሚው ሰው ድርጅቱን ወክሎ ለመፈረም የሚያስችል ሥልጣን ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፤

መ) ማመልከቻው በወኪል አማካይነት የቀረበ ከሆነ የወኪሉ የምዝገባ የምስክር ወረቀትና በአግባቡ የተረጋገጠ የውክልና ሥልጣን ማስረጃ፡፡

**፳፰. ተቃውሞ ማቅረቢያ ጊዜ**

፩/ የንግድ ምልክት እንዳይመዘገብ የሚቀርብ የተቃውሞ ማመልከቻ የተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ ከታተመበት ቀን ጀምሮ በ፷ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

፪/ ጽሕፈት ቤቱ ተቃዋሚው ወገን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ጊዜ ከማለቁ በፊት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ በመፈፀም በጽሁፍ ከጠየቀ የተቃውሞ ማመልከቻ ማቅረቢያ ጊዜውን ለተጨማሪ ፷ ቀናት ሊያራዝምለት ይችላል፡፡

፫/ ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተፈቀደ የመቃወሚያ ጊዜ መራዘሙን የንግድ ምልክት ምዝገባ አመልካቹ እንዲያውቀው ማድረግ አለበት፡፡

**፳፱. በተቃውሞ ማመልከቻ ላይ ውሳኔ ስለመስጠት**

፩/ ጽሕፈት ቤቱ የተቃውሞ ማመልከቻ በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ የማመልከቻውንና የተያያዙ ሰነዶችን ቅጂ ለንግድ ምልክት ምዝገባ አመልካቹ እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፡፡

፪/ ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክት ምዝገባ አመልካቹ ለቀረበው ተቃውሞ በአዋጁ አንቀጽ ፲፫(፫) መሠረት መልስ ሊሰጥ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ ያሳውቀዋል፡፡ ይህም የጊዜ ገደብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተቃውሞ ማመልከቻው እንዲደርሰው ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ከ፺ ቀናት ያነሰ ሊሆን አይችልም፡፡

፫/ የንግድ ምልክት ምዝገባ አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልሱን ካላቀረበ ማመልከቻውን እንደተወው ተቆጥሮ የዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፫(፪) ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆንበታል፡፡

2/ The statement of opposition shall be accompanied by the following:

a) evidences supporting the grounds of opposition;

b) proof of payment of the prescribed fee;

c) if the party opposing the registration is a legal person, copy of the certificate of its registration and evidence authorizing the person who has signed the statement of opposition to represent the legal person;

d) if the statement of opposition is filed through an agent, the certificate of registration of the agent and a duly authenticated power of attorney.

**28. Time for Filing Opposition**

1/ A statement of opposition shall be submitted within 60 days from the date of publication of the notice for call of opposition.

2/ The Office may extend the time of filing a statement of opposition for additional 60 days if the applicant submits written application for extension before expiry of the time specified in sub-article (1) of this Article upon payment of the fee stipulated in the Schedule attached hereto.

3/ The Office shall communicate to the applicant the extension of time for filing opposition granted under sub-article (2) of this Article.

**29. Decision on Opposition**

1/ The Office shall send to the applicant the copy of the statement of opposition and documents accompanying the statement of opposition within 30 days from the date of filing the statement of opposition.

2/ The Office shall notify the applicant with the period fixed for submitting response to the opposition in accordance with Article 13(3) of the Proclamation. Such period may not be less than 90 days from the date the applicant is served with the copy of the statement of opposition in accordance with sub-article (1) of this Article.

3/ If the applicant fails to respond within the time limit specified under sub-article (2) of this Article, the application for registration of the trademark shall be considered as abandoned and be treated in accordance with Article 23(2) of this Regulation.

፬/ ጽሕፈት ቤቱ ለመቃወሚያው የተሰጠው መልስ በቀረበ በ፺ ቀናት ውስጥ በአዋጁ አንቀጽ ፲፫(፬) መሠረት በመቃወሚያው ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፭/ በጽሕፈት ቤቱ ውሳኔ ላይ ከሁለት ባንዱ ወገን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት የይግባኝ ጥያቄ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴ መሠረት ያልቀረበ እንደሆነ ውሳኔው ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**፴. <u>ይግባኝ ስለማቅረብ</u>**

የንግድ ምልክት ምዝገባን በመቃወም የቀረበ ዐ]መልከቻን በተመለከተ በጽሕፈት ቤቱ ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በደረሰው በ፷ ቀናት ውስጥ በአዋጁ አንቀጽ ፲፯(፪) መሠረት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>
## <u>የምዝገባ ሥነ ሥርዓት</u>

**፴፩. <u>የንግድ ምልክትን ስለመመዝገብ</u>**

፩/ ጽሕፈት ቤቱ በንግድ ምልክት ምዝገባው ላይ የቀረበ ወይም ቀርቦ ተቀባይነት ያገኘ ተቃውሞ ከሌለ የንግድ ምልክቱ ለምዝገባ ብቁ መሆኑን በመግለጽ አመልካቹ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ እንዲፈጽም ያሳውቀዋል፡፡

፪/ ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለአመልካቹ በሚልከው ማስታወቂያ ውስጥ በአዋጁ አንቀጽ ፭(፫) ድንጋጌ መሠረት ጥበቃ ሊደረግላቸው በማይችሉ የንግድ ምልክቱ ይዘቶች ላይ አመልካቹ የብቸኛ ተጠቃሚነት መብት እንዳይጠይቅ ለምዝገባው እንደ ቅድመ ሁኔታ ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡

፫/ አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ማስታወቂያ በደረሰው ፺ ቀናት ውስጥ፡-

ሀ) አግባብ ያለውን ክፍያ ከፈጸመ፤ እና

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተቀመጠ ቅደመ ሁኔታን የተቀበለ መሆኑን ከገለጸ፤

ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክቱን ይመዘግባል፡፡

፬/ አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ አግባብ ያለውን ክፍያ ካልፈጸመ ወይም የተጣለውን ቅድመሁኔታ መቀበሉን ካልገለጸ ማመልከቻውን እንደተወው ተቆጥሮ የዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፫(፪) ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆንበታል፡፡

4/ The Office shall render its decision on the opposition pursuant to Article 13(4) of the Proclamation within 90 days from the date of filing the response to the opposition.

5/ The decision of the Office shall be effective if neither of the parties appealed to the court having jurisdiction in accordance with Article 30 of this Regulation.

**30. <u>Appeal</u>**

Any party dissatisfied with the decision of the Office with regard to an opposition to the registration of trademark may, within 60 days from receipt of the decision, appeal to the court having jurisdiction in accordance with Article 17(2) of the Proclamation.

## <u>PART SIX</u>
## <u>REGISTRATION PROCEDURE</u>

**31. <u>Registration of Trademark</u>**

1/ The Office shall, if no opposition is filed or is successful, send notice to the applicant stating the eligibility of the trademark for registration and requesting payment of the fee stipulated in the Schedule attached hereto.

2/ The Office may, in the notice referred to in sub-article (1) of this Article, include a request, as a condition of registration, that the applicant disclaim any exclusive right to the elements in the trademark that are not eligible for protection pursuant to Article 5(3) of the Proclamation.

3/ The Office shall register the trademark if the applicant, within 90 days after being served with the notice referred to in sub-article (1) of this Article:

a) pays the appropriate fee; and

b) accepts the disclaimer requested pursuant to sub-article (2) of this Article.

4/ If the applicant fails to pay the appropriate fee or to accept the condition of disclaimer, within the time limit prescribed under sub-article (3) of this Article, the application for registration of the trademark shall be considered as abandoned and be treated in accordance with Article 23(2) of this Regulation.

## ፴፪. የምዝገባ የምስክር ወረቀት

፩/ ጽሕፈት ቤቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፩ መሠረት የንግድ ምልክትን እንደመዘገበ ለአመልካቹ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚሰጥ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

ሀ) የንግድ ምልክቱን ቅጅ፤

ለ) የምዝገባውን ቀንና ቁጥር፤

ሐ) የባለቤቱን ስም፣ አድራሻና ዜግነት፤

መ) እንደአግባቡ ማመልከቻው ገቢ የሆነበትን ቀን ወይም የቀዳሚነት መብትን ቀን፤

ሠ) ምዝገባው የሚሸፍናቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች እና የምደባ ቁጥራቸውን፤

ረ) ምዝገባው ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ፤

ሰ) አመልካቹ ወኪል ካለው ስምና አድራሻውን፤ እና

ሸ) የብቸኛ ተጠቃሚነት መብት ያለመጠየቅ መግለጫ ተሰጥቶ ከሆነ ይህንኑ፡፡

## ፴፫. ምዝገባን ስለማሳወቅ

፩/ ጽሕፈት ቤቱ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፪ (፪) መሠረት በምዝገባው የምስክር ወረቀት ከተዘረዘሩት መረጃዎች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ መረጃዎች የያዘና የንግድ ምልክቱ የተመዘገበ ስለመሆኑ የሚገልጽ የምዝገባ ማስታወቂያ በአዋጁ አንቀጽ ፲፮ መሠረት እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

፪/ በጽሕፈት ቤቱ የተመዘገበው የንግድ ምልክት ባለቤት ይህን ® ምልክት ከንግድ ምልክቱ ጋር በቅርበት ተያይዞ እንዲታይ በማድረግ የንግድ ምልክቱን መመዝገብ ማስተዋወቅ ይችላል፡፡

## ፴፬. ምትክ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት

፩/ የንግድ ምልክት ምዝገባ የምስክር ወረቀት የጠፋበት ወይም የተበላሸበት የምዝገባ ባለቤት ምትክ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ሊያመለክት ይችላል፡፡

፪/ ጽሕፈት ቤቱ ስለጠፋው የምስክር ወረቀት በአመልካቹ ወጪ ማስታወቂያ በማሳተም ወይም የተበላሸው የምስክር ወረቀት እንዲመለስ በማድረግ እና ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ በማስከፈል ምትክ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

## 32. Certificate of Registration

1/ The Office shall issue a certificate of registration to the applicant upon registering a trademark pursuant to Article 31 of this Regulation.

2/ A certificate of registration to be issued pursuant to sub-article (1) of this Article shall include the following:

a) reproduction of the trademark;

b) the registration date and number;

c) the owner's name, address and nationality;

d) the filing date of the application or right of priority date, as the case may be;

e) the goods or services the registration covers and their classification number;

f) the validity period of the registration;

g) the name and address of applicant's agent, if any; and

h) any disclaimer.

## 33. Notification of Registration

1/ The Office shall, in accordance with Article 16 of the Proclamation, notify the registration which contains same information as it appears on the registration certificate referred to in Article 32 (2) of this Regulation.

2/ The owner of a trademark registered by the Office may publicize the registration by displaying the trademark in close association with the symbol ®.

## 34. Substitute Certificate of Registration

1/ Where a certificate of registration is lost or damaged, the registration owner may apply to the Office for issuance of a substitute certificate.

2/ The Office shall, upon publication of notice, at the expense of the applicant, with regard to a lost certificate or the return of a damaged certificate, and upon payment of the fee prescribed in the Schedule attached hereto, issue a substitute certificate which contains the information stated in the previously issued certificate.

**፴፭. የንግድ ምልክቶች መዝገብ**

፩/ ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክቶች መዝገብ አደራጅቶ ይይዛል፡፡

፪/ ጽሕፈት ቤቱ:-

ሀ) የሚመዘግባቸውን የንግድ ምልክቶች፤

ለ) የሚያድሳቸውን፣ የሚያሻሽላቸውን፣ የሚሰርዛቸውንና ፈራሽ የሚያደርጋቸውን የንግድ ምልክት ምዝገባዎች፤ እና

ሐ) የንግድ ምልክት ባለቤትነት ማስተላለፍንና የፈቃድ ውሎችን፤

የሚመለከቱ መረጃዎችን በንግድ ምልክቶች መዝገቡ ውስጥ መመዝገብ አለበት፡፡

፫/ ጽሕፈት ቤቱ በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት በንግድ ምልክቶች መዝገብ ውስጥ ከሚያስፍራቸው ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች በስተቀር የተመዘገበ የንግድ ምልክትን በተመለከተ በመዝገቡ ውስጥ የሚሠፍሩ መረጃዎች በምዝገባ የምስክር ወረቀቱ ላይ ከሠፈሩት መረጃዎች ጋር ተመሳሳይ መሆን አለባቸው፡፡

**፴፮. የንግድ ምልክቶች ምደባ ሥርዓት**

ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክቶችን የሚመዘግበው ምልክቶችን ለመመዝገብ ዓላማ ተፈጻሚነት የሚኖረውን ዓለም አቀፍ የዕቃዎች እና አገልግሎቶች አመዳደብ ሥርአት በመከተል ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት
## የንግድ ምልክት ምዝገባ እድሳት እና ማሻሻል

**፴፯. የእድሳት ማመልከቻ አቀራረብ**

የንግድ ምልክት ምዝገባ ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ በጽሕፈት ቤቱ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላትና ተገቢው የማመልከቻ ክፍያ መፈጸሙን ከሚያረጋገጥ ማስረጃ ጋር ተያይዞ በአዋጁ አንቀጽ ፳፭(፫) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለጽሕፈት ቤቱ መቅረብ አለበት፡፡

**፴፰. የእድሳት ጥያቄን ስለመቀበል ወይም ውድቅ ስለማድረግ**

፩/ ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክት ምዝገባ እድሳት ማመልከቻን መርምሮ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ሲያገኘው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ አስከፍሎ ምዝገባውን በማደስ ለምዝገባ ባለቤቱ የእድሳት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፪/ ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክት ምዝገባ ዕድሳት ጥያቄው ያልተሟላ ወይም የተሳሳተ ሆኖ ሲያገኘው የእድሳት ማመልከቻውን ያልተቀበለው መሆኑንና ያልተቀበለበትን ምክንያት በመግለጽ ውሳኔውን ለአመልካቹ ያሳውቀዋል፡፡

**35. Register of Trademarks**

1/ The Office shall organize and maintain a Register of Trademarks.

2/ The Office shall enter in the Register information about:

a) trademarks registered by the Office;

b) renewed, amended, canceled and invalidated trademark registrations; and

c) transfer of ownership and license contracts concerning registered trademarks.

3/ Apart from other additional information the Office enters in the Register of Trademarks as provided by the Proclamation and this Regulation, information about a registered mark in the Register of Trademarks shall be the same as shown on the certificate of registration.

**36. Classification System for Trademarks**

The Office shall register trademarks in accordance with the applicable international classification of goods and services with respect to registration of marks.

## PART SEVEN
## RENEWAL AND AMENDMENT OF REGISTRATION OF TRADEMARK

**37. Submission of Application for Renewal**

An application to renew the registration of a trademark shall be submitted to the Office, within the time limit specified in Article 25(3) of the Proclamation, by filling the form prescribed by the Office for such purpose and shall be accompanied with proof of payment of the appropriate application fee.

**38. Acceptance or Refusal of Renewal Request**

1/ If the Office, upon examination of an application for renewal, finds it acceptable, it shall, upon payment of the fee stipulated in the Schedule attached hereto, renew the registration of a trademark and issue certificate of renewal to the registration owner.

2/ If the Office finds that an application for renewal is incomplete or incorrect, it shall refuse the renewal and notify the registration owner of such refusal and the reasons for refusal.

፫/ ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክቱን ምዝገባ ካደሰ በኋላ በምስክር ወረቀቱ ላይ የተገለጹትን መረጃዎች በማካተት የንግድ ምልክቱ የታደሰ ስለመሆኑ ማስታወቂያ ያሳትማል፡፡

## ፴፱. ምዝገባ ቀሪ መሆን

፩/ የንግድ ምልክት ምዝገባ ባለቤት፡-

ሀ) በወቅቱ የእድሳት ጥያቄ ማመልከቻ ያላቀረበ ወይም ተገቢውን ክፍያ ያልፈጸመ እንደሆነ፤ ወይም

ለ) በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፴፰(፪) የተመለከተው ማስታወቂያ በደረሰው ፺ ቀናት ውስጥ በማስታወቂያው የተገለጹትን የእድሳት ጥያቄውን ለመቀበል መሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ) በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፴፰(፪) የተመለከተው ማስታወቂያ በደረሰው ፷ ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ የጽሕፈት ቤቱን ውሳኔ ያላሻረ እንደሆነ፤

የንግድ ምልክት ምዝገባው ቀሪ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

፪/ የንግድ ምልክት ምዝገባ ባለቤቱ፡-

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ለ) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ያልቻለበትን አሳማኝ ምክንያት ጊዜው ከማለፉ በፊት በማቅረብ ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠው በጽሑፍ ካመለከተ፤ እና

ለ) ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተወሰነውን ክፍያ ከፈጸመ፤

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፰(፪) የተገለጹትን የእድሳት ጥያቄውን ለመቀበል መሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ ለማሟላት እንዲችል ጽሕፈት ቤቱ ተጨማሪ የ፺ ቀናት ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡

## ፵. ምዝገባን ስለማሻሻል

፩/ የንግድ ምልክት ምዝገባ በሚከተሉት ምክንያቶች እንዲሻሻል ሊፈቀድ ይችላል፡-

ሀ) በምዝገባው ላይ የተፈጸመ ስህተትን ለማረም፤

ለ) ምዝገባው ከሚሸፍናቸው እቃዎች ወይም አገልግሎቶች ዝርዝር ውስጥ የተወሰኑትን እቃዎች ወይም አገልግሎቶች እና የምደባ ቁጥራቸውን ለመሠረዝ፤

ሐ) የብቸኛ ተጠቃሚነት መብት ያለመጠየቅ መግለጫን ለመመዝገብ፤ ወይም

መ) በምዝገባው ላይ ሌሎች መሠረታዊ ያልሆኑ ለውጦችን ለማድረግ፡፡

3/ The Office shall, after renewal, publish notice of the renewal which shall contain the same information as it appears on the renewal certificate.

## 39. Relinquishment of Registration

1/ The registration of a trademark shall be deemed to be relinquished on the expiry of its period of validity if the registration owner fails:

a) to timely file an application of renewal or to effect the applicable fee;

b) to fully satisfy the conditions for acceptance of the application for renewal specified in the notice referred to in Article 38(2) of this Regulation within 90 days from receipt of the notice; or

c) to obtain a decision of the court having jurisdiction that reverses the decision of the Office upon lodging an appeal within 60 days from receipt of the notice referred to in Article 38(2) of this Regulation.

2/ The Office may grant an extension period of additional 90 days to fully satisfy the conditions for acceptance of the application for renewal specified in the notice referred to in Article 38(2) of this Regulation, if the registration owner:

a) files a written request, prior to the expiry of the period specified under sub-article (1)(b) of this Article, for additional time extension that shows, to the satisfaction of the Office, good cause for the failure to take the required action within the specified period; and

b) pays the fee stipulated in the Schedule attached hereto.

## 40. Amendment of Registration

1/ An amendment to the registration of a trademark may be allowed:

a) to correct a mistake in the registration;

b) to cancel specified goods or services and their classification number covered by the registration;

c) to register a disclaimer; or

d) to make other minor changes in the registration.

፪/ የንግድ ምልክት ምዝገባን ለማሻሻል የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ዓላማ በጽሕፈት ቤቱ የተዘጋጀውን ፎርም በመሙላት፡-

ሀ) በጽሕፈት ቤቱ ምክንያት የተፈጠረን ስህተት ለማሳረም የቀረበ ካልሆነ በስተቀር ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተው ክፍያ መፈጸሙን ከሚያሳይ ማስረጃ፣

ለ) የንግድ ምልክቱን ማሻሻል የሚመለከት ሲሆን ከተሻሻለው የንግድ ምልክት ስዕላዊ መግለጫ ሦስት ኮፒ፣ እና

ሐ) ከምዝገባ የምስክር ወረቀቱ ዋና ቅጅ፣

ጋር ተያይዞ ለጽሕፈት ቤቱ መቅረብ አለበት፡፡

፫/ ጽሕፈት ቤቱ ማመልከቻውን መርምሮ የማሻሻያውን ተገቢነት ሲያረጋግጥ የተደረጉትን ለውጦች በንግድ ምልክቶች መዝገብ ውስጥ በማስፈር ለምዝገባ ባለቤቱ በማሻሻያው ላይ የተመሠረተ አዲስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፣ ሆኖም ማሻሻያው በምዝገባው ላይ የተፈጸመ ስህተትን ለማረም የተደረገ ከሆነ ምዝገባው መጀመሪያ በተፈጸመበት ጊዜ ተስተካክሎ እንደተፈጸመ ምዝገባ ሕጋዊ ውጤት ይኖረዋል፡፡

፬/ ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) በተመለከተው የምዝገባ የምስክር ወረቀት ላይ ከሠፈሩት መረጃዎች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ መረጃዎች የያዘና የንግድ ምልክት ምዝገባው የተሻሻለ ስለመሆኑ የሚገልፅ ማስታወቂያ አሳትሞ ያወጣል፡፡

**፵፩. የወል የንግድ ምልክት አጠቃቀም የሚመራበትን መተዳደሪያ ደንብ ስለማሻሻል**

፩/ ጽሕፈት ቤቱ በአዋጁ አንቀጽ ፳፪(፩) መሠረት ለምዝገባ የቀረበ የወል የንግድ ምልክት አጠቃቀም የሚመራበት መተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያን መመርመርና ለሕዝብ ሰላም ወይም ሥነ ምግባር ተቃራኒ የሆኑ ድንጋጌዎችን ያልያዘ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፪/ በማሻሻያው ላይ ተቃውሞና አስተያየት ለመጋበዝ በአዋጁ አንቀጽ ፳፪(፪) መሠረት የሚወጣው ሕትመት የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

ሀ) የወል የንግድ ምልክቱን ባለቤት ስም፣

ለ) የወል የንግድ ምልክቱን፣

ሐ) ምልክቱ የሚሸፍናቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች፣

መ) የምዝገባውን ቁጥርና ቀን፣

ሠ) የተሻሻለውን የመተዳደሪያ ደንብ ቅጂ፣ እና

ረ) ተቃውሞው ወይም አስተያየቱ መቅረብ የሚችልበትን የጊዜ ገደብ፣ ሆኖም የጊዜ ገደቡ ከሕትመቱ ቀን ጀምሮ ከ፷ ቀናት ያነሰ ሊሆን አይችልም፡፡

2/ An application for amendment of the registration of a trademark shall be submitted to the Office by filling a form prescribed by the Office for such purpose and accompanied by:

a) proof of payment of the fee stipulated in the Schedule attached hereto, except in the case of an amendment to correct a mistake caused by the fault of the Office;

b) in the case of amending the trademark, three copies of a graphical representation of the amended version; and

c) the original certificate of registration.

3/ If the Office, upon examining the application, finds that the proposed amendment is appropriate, it shall enter the changes in the Trademark Register and issue to the registration owner a new certificate of registration based on the amendment; provided, however, that if the amendment is to correct a mistake in the registration, the amended registration shall have the same force and effect as if it had been originally registered in the corrected form.

4/ The Office shall publish notice of amendment of registration which contains same information as it appears on the certificate of registration referred to in sub-article (3) of this Article.

**41. Amendment of Statutes Governing Use of Collective Trademark**

1/ The Office shall review amendments to the statutes governing the use of a collective trademark filed for registration pursuant to Article 22(1) of the Proclamation and determine whether the amendments contain any provision contrary to public order or morality.

2/ Publication of the amendments pursuant to Article 22(2) of the Proclamation shall contain:

a) the name of the owner of the registered collective trademark;

b) the collective trademark;

c) the goods or services covered by the collective trademark;

d) the registration number and date;

e) a copy of the amended statutes; and

f) the time limit for filing opposition and observations; provided, however, that such period may not be less than 60 days from the publication date.

፫/ ጽሕፈት ቤቱ፦

ሀ) ማሻሻያው ለሕዝብ ሰላም ወይም ሥነምግባር ተቃራኒ የሆነ ድንጋጌ አለመያዙን፤ እና

ለ) ምዝገባውን ሊያስከለክል የሚችል ተቃውሞ ወይም አስተያየት ያልቀረበ መሆኑን፤

ሲያረጋግጥ የተሻሻለውን መተዳደሪያ ደንብ መዝግቦ የምዝገባ ማስታወቂያ እንዲታተም ያደርጋል።

፬/ ጽሕፈት ቤቱ የተሻሻለውን መተዳደሪያ ደንብ የምዝገባ ጥያቄ ውድቅ ያደረገው እንደሆነ ውሳኔውን ከነምክንያቶቹ ለምዝገባው ባለቤት ማሳወቅ አለበት።

፭/ በጽሕፈት ቤቱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ የምዝገባ ባለቤት ውሳኔው በደረሰው በ፷ ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

## ክፍል ስምንት
## መብትን ስለመተው እና ምዝገባን ስለመሰረዝና ፈራሽ ስለማድረግ

### ፵፪. መብት ስለመተው

፩/ በተመዘገበ የንግድ ምልክት ላይ ያለ መብትን በመተው ምዝገባውን ለማሠረዝ በአዋጁ አንቀጽ ፴፬(፩) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ተግባር በጽሕፈት ቤቱ በተዘጋጀው ቅጽ ላይ ተሞልቶ መቅረብ አለበት።

፪/ የንግድ ምልክቱ በፈቃድ ውል ለሌላ ሰው እንዲጠቀምበት ተሰጥቶ ከሆነና ይኸው በንግድ ምልክቶች መዝገብ ተመዝግቦ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ በአዋጁ አንቀጽ ፴፬(፪) መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው መስማማቱን በመግለጽ ከሰጠው መግለጫ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።

### ፵፫. ምዝገባን ስለመሰረዝ ወይም ፈራሽ ስለማድረግ

፩/ የንግድ ምልክት ምዝገባን በአዋጁ አንቀጽ ፴፭ ወይም አንቀጽ ፴፮ መሠረት ለማሰረዝ ወይም ፈራሽ ለማስደረግ በሚመለከተው ሰው የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ዓላማ በጽሕፈት ቤቱ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ከደጋፊ ማስረጃዎችና ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተወሰነው ክፍያ መፈጸሙን ከሚያረጋግጥ ማስረጃ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።

፪/ ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻና ደጋፊ ማስረጃዎች ለምዝገባ ባለቤቱ እንዲደርሰው በማድረግ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መልስ እንዲሰጥበት ያሳውቀዋል፤ ሆኖም የሚሰጠው የጊዜ ገደብ ማስታወቂያ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ከ፷ ቀናት ማነስ የለበትም።

3/ The Office shall register the amended statutes and publish notice of registration where it determines that there are no:

a) provisions in the amendments contrary to public order or morality; and

b) oppositions or observations to justify refusal of registration.

4/ If the Office refuses registration of the amended statutes, it shall notify the register owner of its decision and the reasons thereof.

5/ The register owner who is dissatisfied with the decision of the Office may appeal to the court having jurisdiction within 60 days from receipt of the decision.

## PART EIGHT
## RENUNCIATION, CANCELLATION AND INVALIDATION OF REGISTRATION

### 42. Renunciation of Right

1/ An application for registration of renunciation of right on a registered trademark pursuant to Article 34(1) of the Proclamation shall be submitted by filling a form prescribed by the Office for such purpose.

2/ If the trademark has been transferred by license contract and such transfer is entered into the Register of Trademarks, the application referred to in sub-article (1) of this Article shall, pursuant to Article 34(2) of the Proclamation, be accompanied by the written declaration of the licensee consenting to the renunciation.

### 43. Cancellation or Invalidation of Registration

1/ An application requesting the cancellation or invalidation of registration of a trademark pursuant to Article 35 or Article 36 of the Proclamation shall be made in the form prescribed by the Office for such purpose and be accompanied by supporting documents and proof of payment of the fee stipulated by the Schedule attached hereto.

2/ The Office shall send to the registration owner the application and supporting documents submitted to it in accordance with sub-article (1) of this Article together with a notice stating the time limit for submission of a reply; provided, however, that such time limit may not be less than 60 days from the date of receipt of the notice.

፫/ ጽሕፈት ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት የንግድ ምልክት ምዝገባ ፈራሽ ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት መኖሩን ሲረዳ የምዝገባ ባለቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምላሽ እንዲሰጥበት በጽሑፍ ያሳውቀዋል፡፡

፬/ የምዝገባ ባለቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ወይም (፫) መሠረት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልሱን ካላቀረበ ምዝገባውን ለመሠረዝ ወይም ፈራሽ ለማድረግ ያስችላሉ ተብለው የተጠቀሱትን ምክንያቶች እንደተቀበላቸው ተቆጥሮ ጽሕፈት ቤቱ ምዝገባውን የመሠረዝ ወይም ፈራሽ የማድረግ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፭/ የምዝገባ ባለቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ወይም (፫) መሠረት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መልሱን ካቀረበ ጽሕፈት ቤቱ የተነሱትን የክርክር ጭብጦችና የቀረቡለትን ማስረጃዎች በሚገባ መርምሮ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ወይም (፭) መሠረት በጽሕፈት ቤቱ የተሰጠ ውሳኔ ቅጅ ለምዝገባ ባለቤቱና እንደአግባቡ ምዝገባው እንዲሠረዝ ወይም ፈራሽ እንዲሆን ላመለከተው ሰው እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡

፯/ የምዝገባው ባለቤት፡-

ሀ) ጽሕፈት ቤቱ ምዝገባ እንዲሠረዝ ወይም ፈራሽ እንዲሆን የሰጠው ውሳኔ በደረሰው ፷ ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ካላቀረበ፤ ወይም

ለ) ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔውን ካልሻረለት፤

የምዝገባው መሠረዝ ወይም ፈራሽ መሆን በንግድ ምልክቶች መዝገብ እንዲሠፍርና በማስታወቂያ ታትሞ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ
## ስለባለቤትነት መተላለፍ እና ስለፈቃድ ውል

### ፵፬. የባለቤትነት መተላለፍን እና የፈቃድ ውልን ስለመመዝገብ

፩/ የተመዘገበ የንግድ ምልክት ባለቤትነት መተላለፍን ወይም የፈቃድ ውልን ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ዓላማ በጽሕፈት ቤቱ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ከባለቤትነት ማስተላለፊያ ስምምነት ሰነዱ ወይም ከፈቃድ ውሉ ቅጅና ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተወሰነው ክፍያ መፈጸሙን ከሚያረጋግጥ ማስረጃ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡



3/ If the Office, on its own initiative, determines the existence of a ground to justify invalidation of the registration of a trademark, it shall communicate same, in writing, to the registration owner and solicit him to reply within the time limit prescribed in sub-article (2) of this Article.

4/ If the registration owner fails to respond in accordance with sub-article (2) or (3) of this Article within the prescribed period, the grounds alleged to justify cancellation or invalidation of the registration shall be deemed to be admitted and the Office shall decide to cancel or invalidate the registration.

5/ If the registration owner submits its reply in accordance with sub-article (2) or (3) of this Article within the prescribed period, the Office shall render its decision upon properly examining the issues raised and the evidences produced.

6/ Copies of the decision of the Office rendered pursuant to sub-article (4) or (5) of this Article shall be sent to the registration owner and, as may be applicable, to the person who has requested the cancellation or invalidation of the registration.

7/ If the registration owner fails:

a) to lodge an appeal with the court having jurisdiction within 60 days from the date of receipt of a copy of the decision of the Office to cancel or invalidate the registration of a trademark; or

b) to obtain a decision of reversal by the court;

a notice of the cancellation or invalidation of the registration shall be entered into the Register of Trademarks and shall be published.

## PART NINE
## TRANSFER OF OWNERSHIP AND LICENSE CONTRACT

### 44. Registration of Transfer of Ownership or License Contract

1/ An application for the registration of transfer of ownership or license contract of a registered trademark shall be made by filling the form prescribed by the Office for such purpose and be accompanied by a copy of the transfer agreement or the license contract and proof of payment of the applicable fee prescribed in the Schedule attached hereto.

፪/ ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ማመልከቻ ተሟልቶ ሲቀርብለት ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች በንግድ ምልክቶች መዝገብ ላይ ማስፈርና የምዝገባ ማስታወቂያ ማሳተም አለበት፦

ሀ) ባለቤትነት የተላለፈለትን ወይም የፈቃድ ውል የተሰጠውን ሰው ሙሉ ስም፣ አድራሻና ዜግነት፤

ለ) የባለቤትነት መተላለፉ ወይም የፈቃድ ውሉ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ዝርዝርና ምደባቸውን፤

ሐ) ባለቤትነት በተላለፈበት ስምምነት ወይም በፈቃድ ውሉ መሠረት የንግድ ምልክቱ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችልበትን ጂኦግራፊያዊ ክልል፤ እና

መ) የባለቤትነት መተላለፉ ወይም የፈቃድ ውሉ የተመዘገበበትን ቀን።

፫/ የባለቤትነት መተላለፉ ወይም የፈቃድ ውሉ የሚመለከተው በንግድ ምልክቱ ምዝገባ ከተሸፈኑት እቃዎች ወይም አገልግሎቶች ውስጥ የተወሰኑትን ብቻ ከሆነ ጽሕፈት ቤቱ የነዚህኑ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ዝርዝር የያዘ አዲስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ባለቤትነቱ ለተላለፈለት ሰው ወይም ይህንኑ የሚያሳይ ማስረጃ ለባለፈቃዱ ይሰጣል።

### ፵፭. የፈቃድ ውል መሰረዝን ስለመመዝገብ

፩/ የተመዘገበ የንግድ ምልክት የፈቃድ ውል መሠረዝን ለማስመዝገብ የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ዓላማ በጽሕፈት ቤቱ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት የፈቃድ ውሉን ከሰረዘው ሰነድ ቅጅና ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተወሰነው ክፍያ መፈጸሙን ከሚያረጋግጥ ማስረጃ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።

፪/ ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ማመልከቻ ተሟልቶ ሲቀርብለት የፈቃድ ውሉ ስለመሰረዙ በንግድ ምልክቶች መዝገብ ላይ ማስፈርና የምዝገባውን መሰረዝ የሚመለከት ማስታወቂያ ማሳተም አለበት።

## ክፍል አሥር
## ስለመከፋፈል፣ ስለማዋሃድ እና ተከታታይነት ስላላቸው የንግድ ምልክቶች

### ፵፮. ማመልከቻን ስለመከፋፈል

፩/ ማንኛውም አመልካች የንግድ ምልክት ምዝገባው ከመከናወኑ በፊት በማናቸውም ጊዜ ማመልከቻው በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ የተለያዩ ማመልከቻዎች እንዲከፋፈል በጽሕፈት ቤቱ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ማመልከት ይችላል።

2/ The Office shall, upon receipt of duly completed application, enter into the Register of Trademarks information containing at least the following particulars and publish notice of the registration:

a) the full name, address and the nationality of the transferee or the licensee;

b) the list of goods or services and their classification subject to the ownership transfer or license contract;

c) the geographic area where the trademark is to be used in accordance with the transfer agreement or license contract;

d) date of registration of the transfer or license contract.

3/ If the transfer of ownership or license contract is for only certain goods or services covered by the registration of the trademark, the Office shall issue a new certificate of registration to the transferee or an evidence to the licensee by listing the goods or services covered by the transfer or license contract.

### 45. Registration of Cancellation of License Contract

1/ An application for the registration of cancellation of a license contract of a registered trademark shall be made by filling the form prescribed by the Office for such purpose and be accompanied by a copy of the document cancelling the license contract and proof of payment of the applicable fee prescribed in the Schedule attached hereto.

2/ The Office shall, upon receipt of duly completed application, enter into the Register of Trademarks information about the cancellation of the license contract and publish notice of cancellation of the registration.

## PART TEN
## DIVISION, MERGER AND SERIES OF MARKS

### 46. Division of Application

1/ An applicant may file a request, at any time before the registration of a trademark, using the form prescribed by the Office for such purpose, for a division of his application into two or more separate applications.

፪/ አመልካቹ እያንዳንዱ የተከፋፈለው ማመልከቻ የሚሸፍናቸውን የዕቃዎች ወይም የአገልግሎቶች ዝርዝር መግለጽ አለበት፡፡

፫/ የክፍፍሉ ውጤት የሆነው እያንዳንዱ ማመልከቻ የመጀመሪያውን ማመልከቻ ቀን እንደያዘ ሆኖ እንደተለያየ ማመልከቻ ይስተናገዳል፡፡

፬/ ማመልከቻ ለመከፋፈል ጥያቄ የቀረበው ማመልከቻው ከታተመ በኋላ ከሆነ በመጀመሪያው ማመልከቻ ላይ የቀረበው ተቃውሞ የክፍፍሉ ውጤት በሆነው በእያንዳንዱ ማመልከቻ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**፵፯. የተለያዩ ማመልከቻዎችን ስለማዋሃድ**

፩/ የተለያዩ ማመልከቻዎችን ያቀረበ አመልካች ጽሕፈት ቤቱ ማናቸውንም ማመልከቻ የማሳተም ዝግጅቱን ከማጠናቀቁ በፊት በማንኛውም ጊዜ በጽሕፈት ቤቱ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ማመልከቻዎቹ እንዲዋሃዱ ማመልከት ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የማዋሃድ ጥያቄ የቀረበባቸው ማመልከቻዎች፡-

ሀ) አንድ ዓይነት የንግድ ምልክትን የሚመለከቱ ከሆነ፤

ለ) አንድ ዓይነት የማመልከቻ ቀን ካላቸው፤ እና

ሐ) የውህደት ጥያቄው በቀረበበት ወቅት በአንድ ሰው ስም ተይዘው የሚገኙ ከሆነ፤

ጽሕፈት ቤቱ ጥያቄውን ተቀብሎ ወደአንድ ማመልከቻነት ያዋህዳቸዋል፡፡

**፵፰. የተለያዩ ምዝገባዎችን ስለማዋሃድ**

፩/ የሁለት ወይም ከዚያ በላይ የንግድ ምልክት ምዝገባዎች ባለቤት የሆነ ሰው ምዝገባዎቹ ወደ አንድ ምዝገባ እንዲዋሃዱ በጽሕፈት ቤቱ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ማመልከት ይችላል፡፡

፪/ ምዝገባው አንድ ዓይነት የንግድ ምልክትን የሚመለከት ከሆነ ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የቀረበውን ጥያቄ ተቀብሎ የተለያዩትን ምዝገባዎች ወደ አንድ ምዝገባ ያዋህዳል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከሚዋሃዱት ምዝገባዎች አንዱ የብቸኝነት መብትን ያለመጠየቅ መግለጫ የያዘ ከሆነ ይኸው ገደብ በተዋሃደው ምዝገባም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፬/ የተዋሃዱት ምዝገባዎች የተለያየ የምዝገባ ቀናት ከኖራቸው ከምዝገባ ቀኖቹ ውስጥ የቅርብ ጊዜ የሆነው የተዋሃደው ምዝገባ ቀን ይሆናል፡፡

2/ The applicant shall indicate for each division the specification of goods or services.

3/ Each divisional application shall be treated as a separate application for registration with the same filing date as the original application.

4/ Where the request to divide an application is filed after publication of the application, any opposition to the original application shall apply to each divisional application.

**47. Merger of Separate Applications**

1/ An applicant who has made separate application for registration of a trademark may, at any time before preparation for the publication of any of the applications have been completed by the Office, file a request, using the form prescribed by the Office for such purpose, to merge the separate applications into a single application.

2/ The Office shall accept the request made under sub-article (1) of this Article and merge the applications into a single application if all the applications which are the subject of the request for merger:

a) are in respect of the same trademark;

b) bear the same date of application; and

c) are, at the time of the request, in the name of the same person.

**48. Merger of Separate Registrations**

1/ The owner of two or more registrations of a trademark may request the Office, by filling the form prescribed by the Office for such purpose, to merge them into a single registration.

2/ The Office shall accept the request made under sub-article (1) of this Article and merge them into a single registration if the registration is in respect of the same trademark.

3/ Where any registration of a trademark to be merged under sub-article (1) of this Article is subject to a disclaimer, the merged registration shall also be subject to the same limitation.

4/ The date of registration of the merged registration shall, where the separate registrations bear different dates of registration, be the latest of those dates.

**፵፱. ተከታታይነት ስላላቸው የንግድ ምልክቶች ምዝገባ**

፩/ ተከታታይነት ያላቸው የንግድ ምልክቶች ባለቤት የሆነ ሰው የንግድ ምልክቶቹ በአንድ ምዝገባ ውስጥ ተከታታይ ሆነው እንዲመዘገቡለት በጽሕፈት ቤቱ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ማመልከት ይችላል።

፪/ ተከታታይ የተባለው የእያንዳንዱ የንግድ ምልክት ስዕላዊ መግለጫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከሚቀርበው ማመልከቻ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።

፫/ ጽሕፈት ቤቱ የንግድ ምልክቶቹ ተከታታይነት ያላቸው መሆናቸውን ሲያምን ማመልከቻውን ተቀብሎ ተከታታይ አድርጎ ይመዘግባቸዋል።

**፶. ተከታታይነት ያላቸው የንግድ ምልክቶች ማመልከቻን ስለመከፋፈል**

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፵፱ መሠረት ተከታታይነት ያላቸው የንግድ ምልክቶችን ለማስመዝገብ ማመልከቻ ያቀረበ ሰው ጽሕፈት ቤቱ ማመልከቻውን የማሳተም ዝግጅቱን ከማጠናቀቁ በፊት በማንኛውም ጊዜ በጽሕፈት ቤቱ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ማመልከቻው በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የተለያዩ ማመልከቻዎች እንዲከፋፈል ማመልከት ይችላል።

፪/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፵፮(፪) የተደነገገው ሁኔታ ከተሟላ ጽሕፈት ቤቱ ጥያቄውን ተቀብሎ ማመልከቻውን ይከፋፍለዋል።

## ክፍል አሥራ አንድ
## ስለንግድ ምልክት ወኪሎች

**፶፩. ምዝገባ**

፩/ ከንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ ሂደት ጋር በተያያዘ የንግድ ምልክት ባለቤቶችን የመወከል አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በንግድ ምልክት ወኪልነት መመዝገብ አለበት።

፪/ በንግድ ምልክት ወኪልነት በጽሕፈት ቤቱ ለመመዝገብ የሚፈልግ አመልካች፡-

ሀ) መኖሪያ አድራሻው በኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ፤

ለ) ዕድሜው ቢያንስ ፳፩ ዓመት የሞላው፤

ሐ) በኢትዮጵያ ውስጥ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ያለው ጠበቃ ወይም አግባብ ባለው ዘርፍ ቢያንስ መካከለኛ የትምህርት ደረጃ ያለው፣ ከንግድ ምልክት ጋር የተያያዘ ከሦስት ዓመት ያላነሰ ልምድ ያለውና በጽሕፈት ቤቱ የሚሰጠውን የብቃት መመዘኛ ያለፈ ሰው፤ እና

**49. Registration of Series of Trademarks**

1/ The owner of a series of trademarks may apply to the Office, by filling a form prescribed by the Office for such purpose, for their registration as a series in a single registration.

2/ A graphic representation of each trademark claimed to be in the series shall be included in the application made under sub-article (1) of this Article.

3/ The Office shall, if satisfied that the marks constitute a series, accept the application and register them accordingly.

**50. Division of Application for Registration of Series of Trademarks**

1/ A person who applied for registration of a series of trademarks pursuant to Article 49 of this Regulation may, at any time before preparations of publication have been completed by the Office, request the division of the application into two or more separate applications by filling a form prescribed by the Office for such purpose.

2/ If the conditions provided under Article 46(2) of this Regulation are met, the Office shall accept the request and divide the application accordingly.

## PART ELEVEN
## TRADEMARK AGENTS

**51. Registration**

1/ Any person who wants to act as agent of trademark owners in connection with proceedings of registration and protection of trademarks shall be registered as a trademark agent.

2/ An applicant who wants to be registered by the Office as a trademark agent shall:

a) reside in Ethiopia;

b) be at least 21 years of age;

c) be an attorney authorized to practice law in Ethiopia, or be a person who has acquired at least middle level qualification in the relevant field of study, has a work experience in the area of trademark for not less than three years and has passed the competence assessment evaluation administered by the Office; and

መ) ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ወይም በሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል የተሰጠ የወንጀል ወይም የሙያ ሥነ-ምግባር ጉድለት ውሳኔ ሪከርድ የሌለበት፤

መሆን አለበት።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (መ) የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ማንኛውም ሰው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ በመፈፀም ለንግድ ምልክት ወኪሎች የሚሰጠውን የብቃት መመዘኛ መውሰድ ይችላል።

፬/ ጽሕፈት ቤቱ ለንግድ ምልክት ወኪሎች የሚሰጠውን የብቃት መመዘኛ በመመሪያ በሚወሰነው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰጣል።

## ፶፪. የምዝገባ ምስክር ወረቀት

፩/ ጽሕፈት ቤቱ የምዝገባ ማመልከቻው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፶፩ የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ሆኖ ሲያገኘው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ በማስከፈል የአመልካቹን ስም በንግድ ምልክት ወኪሎች መዝገብ በማስፈር የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል።

፪/ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ፡-

ሀ) የንግድ ምልክት ወኪሉን ሙሉ ስም፣ ዜግነት እና የመኖሪያና የሥራ አድራሻ፤

ለ) የምዝገባውን ቀን፤ እና

ሐ) የምዝገባ የምስክር ወረቀት ሰጪውን ኃላፊ ስምና ፊርማ ፤

የሚያካትት ይሆናል።

፫/ የንግድ ምልክት ወኪል የምስክር ወረቀት ጸንቶ የሚቆየው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት ይሆናል።

## ፶፫. የምዝገባ ዕድሳት

፩/ የንግድ ምልክት ወኪል ምዝገባን ለማሳደስ የሚቀርብ ማመልከቻ በጽሕፈት ቤቱ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን ፎርም በመሙላት ምዝገባው ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ካበቃ በኋላ ባሉት ፴ ቀናት ውስጥ ለጽሕፈት ቤቱ መቅረብ አለበት።

፪/ ጽሕፈት ቤቱ የእድሳት ማመልከቻ ሲቀርብለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፶፩(፪) ተራ ፊደል (ሀ) እና (መ) የተመለከቱት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ክፍያ በማስከፈል ምዝገባውን አድሶ የዕድሳት የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

d) have no record of conviction for criminal offence or professional misconduct by the court having jurisdiction or relevant regulatory body.

3/ Any person fulfilling the requirements stipulated from paragraph (a) to (d) of sub-article (2) of this Article may take trademark agents' competence assessment, upon payment of the fee prescribed in the Schedule attached hereto.

4/ The Office shall conduct trademark agents' competence assessment twice a year in accordance with the time schedule specified by its directive.

## 52. Certificate of Registration

1/ Where the Office ascertains that an application complies with the requirements specified under Article 51 of this Regulation, it shall enter the applicant's name in the Register of Trademark Agents and issue a certificate of registration, upon payment of the fee prescribed in the Schedule attached hereto.

2/ The certificate of registration shall include the following particulars:

a) the full name, nationality and residential and business addresses of the trademark agent;

b) the date of registration; and

c) name and signature of the issuing officer.

3/ A certificate of registration of a trademark agent shall be valid for one year from the date of issuance.

## 53. Renewal of Registration

1/ An application for renewal of registration of a trademark agent shall be submitted to the Office, within 30 days after the expiry of its validity, by filling the form prescribed by the Office for such purpose.

2/ Where the Office receives an application for renewal, it shall, subject to the requirements stipulated under paragraph (a) and (d) of Article 51(2) of this Regulation and upon payment of the fee prescribed in the Schedule attached hereto, renew the registration and issue a certificate of renewal.

፫/ የእድሳት ማመልከቻው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረበ በሚቀጥሉት ፴ ቀናት ውስጥ ሊቀርብና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፶፮(፫) መሠረት የሚወሰነው ተጨማሪ ክፍያ ተፈጽሞ ሊታደስ ይችላል፡፡

**፶፬. <u>የተመዘገቡ የንግድ ምልክት ወኪሎችን ዝርዝር ስለማሳተም</u>**

ጽሕፈት ቤቱ የተመዘገቡ የንግድ ምልክት ወኪሎችን ዝርዝር በየዓመቱ ያሳትማል፡፡

**<u>ክፍል አሥራ ሁለት</u>**
**<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>**

**፶፭. <u>መረጃ ስለመጠየቅና ማግኘት</u>**

ማንኛውም የሚመለከተው ሰው ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ መሠረት የተወሰነውን ክፍያ በመፈጸም፦

፩/ የንግድ ምልክት ፍለጋ ተደርጎ የፍለጋ ሪፖርቱ እንዲሰጠው፤ ወይም

፪/ የንግድ ምልክቶች መዝገብን ወይም በጽሕፈት ቤቱ ለሕዝብ ክፍት የተደረጉ ሌሎች ሪከርዶችንና ሰነዶችን ለመመልከትና ቅጂዎቻቸው እንዲሰጡት፤

በጽሑፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**፶፮. <u>የአገልግሎት ክፍያዎች</u>**

፩/ በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ጽሕፈት ቤቱ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚፈጸሙ ክፍያዎች ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከቱት ተመኖች መሠረት ይከፈላሉ፡፡

፪/ የሚሰጠው አገልግሎት ምድባቸው ከአንድ በላይ የሆነ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን የሚሸፍን የንግድ ምልክትን የሚመለከት ሲሆን ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ምድብ በሠንጠረዡ የተመለከተው ክፍያ ፶ በመቶ በተጨማሪነት ይከፈላል፡፡

፫/ በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ የተወሰነው መደበኛው የማሳደሻ ጊዜ ካለፈ በኋላ ዘግይቶ ለሚፈጸም ማንኛውም የምዝገባ እድሳት በሠንጠረዡ የተመለከተው አግባብ ያለው ክፍያ ፶ በመቶ በተጨማሪነት ይከፈላል፡፡

**፶፯. ስለጊዜ ገደቦች አቆጣጠር**

በአዋጁ ወይም በዚህ ደንብ የተመለከተ የጊዜ ገደብ የሚያበቃበት ቀን በሥራ ቀን ላይ ያልዋለ እንደሆነ ገደቡ የሚያበቃው በሚቀጥለው የሥራ ቀን ይሆናል፡፡

3/ Where an application for renewal is not submitted within the period specified under sub-article (1) of this Article, the registration may be renewed if the application is submitted within the next 30 days and upon payment of additional fee as determined pursuant to Article 56(3) of this Regulation.

**54. <u>Publication of List of Registered Trademark Agents</u>**

The Office shall annually publish the list of registered trademark agents.

**<u>PART TWELVE</u>**
**<u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>**

**55. <u>Access to Information</u>**

Any interested person may, upon payment of the fees prescribed in the Schedule attached hereto, request in writing:

1/ for search of a trademark and to obtain a search report; or

2/ to inspect the Register of Trademarks or other records and documents made public by the Office and to obtain copies thereof.

**56. <u>Fees</u>**

1/ Payments of fees to be made for the services of the Office pursuant to the Proclamation and this Regulation shall be effected in accordance with the rates prescribed in the Schedule attached hereto.

2/ Where the trademark subject to a service covers more than one class of goods or services the fee shall include additional payment of 50% of the fee stipulated in the Schedule with respect to each subsequent class of goods or services.

3/ In the case of late renewal of any registration after the expiry of the regular renewal period specified under the Proclamation or this Regulation, additional payment of fee equivalent to 50% of the applicable fee stipulated in the Schedule attached hereto shall be required.

**57. <u>Computation of Deadlines</u>**

When a deadline specified in the Proclamation or this Regulation falls on a day other than a working day, the next working day hereto shall be taken as the deadline.

## ፶፰. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

፩/ ይህ ደንብ ከጸናበት ቀን በፊት ቀርበው በመታየት ላይ ያሉ የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻዎች ሲሠራበት በቆየው ሥርዓት መሠረት ፍጻሜ ያገኛሉ፤ ሆኖም ገና ያልተፈጸሙ የአገልግሎት ክፍያዎችን በሚመለከት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተወሰኑት ተመኖች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

፪/ ይህ ደንብ ከጸናበት ቀን በፊት የተመዘገቡ የንግድ ምልክት ወኪሎች ጽሕፈት ቤቱ በመመሪያ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በዚህ ደንብ የተደነገጉትን መስፈርቶች አሟልተው እንደገና መመዝገብ አለባቸው።

## ፶፱. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ጽሕፈት ቤቱ አዋጁንና ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

## ፷. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፭ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## 58. Transitory Provisions

1/ Pending applications for trademark registrations prior to the effective date of this Regulation shall be treated in accordance with the previously existing procedures; provided, however, that the fees prescribed in the Schedule attached hereto shall be applicable with respect to outstanding payments of fees.

2/ Trademark agents registered prior to the effective date of this Regulation shall be re-registered upon fulfillment of the requirements provided under this Regulation within the period determined by directive of the Office.

## 59. Power to Issue Directive

The Office may issue directives necessary for the implementation of the Proclamation and this Regulation.

## 60. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 24th day of December, 2012.

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

## ሠንጠረዥ

## የአገልግሎት ክፍያዎች

| ተ.ቁ | የአገልግሎቱ ዓይነት | ክፍያ (ብር) |
|---|---|---|
| ፩ | ለንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ | ፩ሺ፯፻፶ |
| ፪ | ለንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻ ማሻሻያ | ፫፻፶ |
| ፫ | ለንግድ ምልክት ምዝገባ መቃወሚያ | ፩ሺ፭፻ |
| ፬ | ለንግድ ምልክት ምዝገባ | ፫ሺ |
| ፭ | ለንግድ ምልክት ምዝገባ ዕድሳት ማመልከቻ | ፩ሺ፫፻ |
| ፮ | ለንግድ ምልክት ምዝገባ ዕድሳት | ፪ሺ፪፻ |
| ፯ | ለንግድ ምልክት ምዝገባ ማሻሻያ ማመልከቻ | ፫፻፶ |
| ፰ | ለንግድ ምልክት ምዝገባ ማሻሻያ | ፫፻፹ |
| ፱ | ለንግድ ምልክት ምዝገባ ምትክ የምስክር ወረቀት | ፬፻፺፭ |
| ፲ | ለንግድ ምልክት ምዝገባ የማስረዝ ወይም ፈራሽ የማስደረግ ማመልከቻ | ፪ሺ፯፻ |
| ፲፩ | ለንግድ ምልክት ባለቤትነት መተላለፍ ምዝገባ | ፩ሺ፫፻ |
| ፲፪ | ለንግድ ምልክት የፍቃድ ውል ምዝገባ | ፩ሺ፫፻ |
| ፲፫ | ለንግድ ምልክት ፈቃድ ውል መሠረዝ ምዝገባ | ፬፻፶ |
| ፲፬ | የንግድ ምልክት ምዝገባ ማመልከቻዎችን ለመከፋፈል (የክፍፍሉ ውጤት ለሆነው ለእያንዳንዱ ማመልከቻ) | ፫፻፶ |
| ፲፭ | የንግድ ምልክት ምዝገባዎችን ወይም የምዝገባ ማመልከቻዎችን ለማዋሀድ (ለእያንዳንዱ ምዝገባ ወይም ማመልከቻ) | ፫፻፶ |
| ፲፮ | ለንግድ ምልክት ወኪል ምዝገባ ማመልከቻ. | ፫፻፲፭ |
| ፲፯ | ለንግድ ምልክት ወኪሎች ብቃት መመዘኛ | ፪፻፸ |
| ፲፰ | ለንግድ ምልክት ወኪል ምዝገባ | ፩ሺ፫፻፶ |
| ፲፱ | ለንግድ ምልክት ወኪል ምዝገባ ዕድሳት | ፩ሺ፩፻፳፭ |
| ፳ | ለጊዜ ገደብ ማራዘሚያ ማመልከቻ | ፭፻ |
| ፳፩ | ለተመዘገቡ የንግድ ምልክቶች የማጣራት ፍለጋ | ፬፻፶ |
| ፳፪ | የጽሕፈት ቤቱን ሪከርዶችና ሰነዶች ለመመልከት | ፩፻፶ |
| ፳፫ | ለሪከርዶችና ሰነዶች ቅጂ (በገጽ) | ፲ |

## SCHEDULE

## SERVICE FEES

| No. | Types of Service | Fees (Birr) |
|---|---|---|
| 1 | Application for Registration of Trademark | 1750.00 |
| 2 | Amendment of Application for Registration Trademark | 350.00 |
| 3 | Opposition to Registration of a Trademark | 1500.00 |
| 4 | Registration of Trademark | 3000.00 |
| 5 | Application for Renewal of Registration of a Trademark | 1300.00 |
| 6 | Renewal of Registration of a Trademark | 2200.00 |
| 7 | Application for Amendment of Registration of a Trademark | 350.00 |
| 8 | Amendment of Registration of a Trademark | 360.00 |
| 9 | Substitute Certificate of Registration of a Trademark | 495.00 |
| 10 | Application for the cancellation or invalidation of the Registration of a Trademark | 2600.00 |
| 11 | Registration of Transfer of Ownership of a Trademark | 1300.00 |
| 12 | Registration of License Contract of a Trademark | 1300.00 |
| 13 | Registration of Cancellation of License Contract of a Trademark | 450.00 |
| 14 | Division of Application for Registration of a Trademark( (for each application resulting from the division) | 350.00 |
| 15 | Merger of Registration or applications for Registration of a Trademark (for each registration or application) | 350.00 |
| 16 | Application for Registration of a Trademark Agent | 315.00 |
| 17 | Trademark Agents' Competence Assessment | 270.00 |
| 18 | Registration of a Trademark Agent | 1350.00 |
| 19 | Renewal of Registration of a Trademark Agent | 1125.00 |
| 20 | Application for Extension of a Time Limit | 500.00 |
| 21 | Search for Registered Trademarks | 450.00 |
| 22 | Inspection of Records and Documents of the Office | 150.00 |
| 23 | Copies of Records and Documents of the Office (per page) | 10.00 |